# Repentance In Ramadan

# ተውባ በረመዷን



በወጣቱ ተልዕኮ(አህመድ የሱፍ)

## Presented by: Youth-Mission Online Books Publishing.

# Repentance In Ramadan

# ተውባ በረመዷን

## በወጣቱ ተልዕኮ(አህመድ የሱፍ)

**All right reserved**

© የወጣቱ ተልዕኮ

የወጣቱ ተልዕኮ ኦንላይን እትም 2008

ሰሜን ወሎ ወልዲያ

ahmedyesuf29@gmail.com

+251927790323

http://youth-mission.mobie.in

ተውባ___አሏህ ለባሮቹ ከዋለው ትልቅ ችሮታ አንዱ ነው። በቅንነት ወደ እሱ ለተመለሱ ባሮቹ ወንጀሎቻቸውን በመማር መጥፎ ስራዎቻቸውን ወደ መልካም ስራ የሚቀይርላቸው መሆኑ ቃል የገባበት ነው።

በዛ ላይ ረመዷን __የጀሃነም በሮች ተዘግተው የጀነት በሮች የሚከፈቱበት ፣ ሸይጧን የሚታሰርበት ፣ ከሽ ወራቶች በላይ በላጭ የሆነችን ለሊት የያዝ ፣ ቀርአን የወረደበት ፣ የአሏህ እዝነት ያለሂሳብ የሚዘንብበት ነው። ለውጥን ካሰቡ አይቀር ይህኔ ነው።

# ተውባ በረመዷን

## በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

## በወጣቱ ተልዕኮ(አህመድ የሱፍ)

የመልካምነትን መንገድ ላቀረበልንና የተውበት(የንሰሃ) በርን ለከፈተልን አሏህ ምስጋና ይገባው። የአሏህ በረካና ሰላም በመልዕክተኛው ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ፣ በቤተሰቦቻቸውና የሳቸውን ፈለግ በተከተሉ ላይ ሁሉ ይሁን።

ይህ ወር የአምላካችን ውዴታ የምናገኝበት በዱንያም በአኺራም ደስታን የምንጎናፀፍበት ፣ ሁኔታችንን እና ተግባራችንን የምንቀይርበት ያድርግልን። ይህችን ጽሑፍ ያነበብን ሁሉ የምንጠቀምባት ያድርግልን። አሏህ ግልፅም ድብቅም የሆነ ወንጀላችንን ሁሉ ይማርልን።

ውድ ሙስሊም እህት ወንድሞቼ ይህ የተባረከ ፣ የልግስና ፣ የመልካምነትና የደግነት ወር መቷልና እንኳን ደስ አላችሁ እንኳን ደስ አለን።

በትርሚዚና በኢብን ማጃ በተዘገበው ሐዲስ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) የረመዷን የመጀመሪያው ሌሊት በመጣ ጊዜ ሰይጣናቶች ተጠፍረው ይታሰራሉ። የጀሃነም በሮች ይዘጋሉ፤ አንዷትም በር አትከፈትም። የጀነት በሮች ይከፈታሉ፤ አንድም በር አይዘጋም። ተጣሪው "መልካም ፈላጊ ሆይ! ወደ አሏህ ና መጥፎ ፈላጊ ሆይ! (መጥፎን ነገር) ተው አሏህ ሰዎችን ከጀሃነም እሳት ያወጣልና" ሲል ይጣራል ብለዋል።

ረመዷን መቷልና አሏህን ፈርተን ተፀፅተን እያለቀስን ወደ እሱ እንመለስ። ምህረቱን

እንለምነው። በዚህ ወር ካልተማርን ፣ በሰራናቸው ሃጢያት ካላለቀስን ፣ እራሳችንን ከአሏህ ፊት ዝቅ ካለደረግን እና መቼ ይሆን የምንመለሰው?

ውድ ሙስሊም እህት ወንድሞቼ ለምን ይሆን አንዴኳ አምላክልችነን ፈርተን የማናለቅሰው? በዚህ ወር ልባችን ወደ አሏህ እንደቀረበች አይሰማችሁም? ወደ አምላካችን አሏህ የበለጠ በመተናነስ ፣ በተውባ ፣ በታዛዥነት የምንቀርብበት እድል እንደሆነ አይሰማንም? አሏሁ አዘወጀል እንዲህ ሲል ይገስፀናል፦

**=<({አል-ቁርአን 82:6})>=**

**{6} አንተ ሰው ሆይ! ስለ ቸሩ ጌታህ ምን ግዴለሽ አደረገህ?**

በእርግጥም ስለጌታችን ምን ግዴለሽ አድርጎን እሱን ባለመታዘዝ አመፅን? እንዴትስ ገደቡን አለፍን? ምናልባት የአሏህን ሰፊ ችሮታ ችላ ብለን ይሆን? ወይስ ሃያልነቱን ሁሌም የሚያየን መሆኑን ዘነጋን? እህት ወንድሞቼ ወንጀላችን ምን ያህል ትንሽ መሆኑን ሳይሆን የምናምፀው አሏህ ምን ያህል ታላቅ መሆኑን እንመለከት።

አሏህ በቁርአኑ አመፆኞችን ወደ እሱ በማስጠጋት ባሮቼ ሆይ! ብሎ በመጥራት የምስራችና የለውጥ ቃልኪዳን ገብቶልናል። ይህ የሚሆነው ግን አሏህ እንዳለው በነፍሶቻችን ውስጥ ያለውን ነገር እስከቀየርን ድረስ ነው።

**=<({አል-ቁርአን 39:53})>=**

**{53} በላቸው! እናንተ በነፍሶቻችሁ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአሏህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ። በእርግጥ አሏህ ሃጥያቶችን በሙሉ ይምራልና። እነሆ እሱ አዛኝ መሃሪ ነው።**

**=<({አል-ቁርአን 25:70})>=**

***{70}.....እነዚያ የተፀፀቱና ያመኑ መልካም ስራም የሰሩ ለእነሱ አሏህ ወንጀሎቻቸውን ወደ መልካም ስራ ይቀይርላቸዋል። አሏህ እጅግ መሃሪ አዛኝ ነው።***

ይህ አምላካችን አሏህ ወንጀሎቻችነን ወደ መልካም ስራዎች የሚቀይርልን ታላቅ የምስራች ታላቅ በረካ ታላቅ ችሮታ ነው። በእርግጥ አሏህ ታላቅ ነው። እንዲህ አይነቱን ችሮታ ማንም አያጣውም ደንቆሮና ለዚህ በረካ ግድ የሌለው ሰው ሲቀር። ሆኖም ይህን ችሮታ ለማግኘት ከፈለግን አሏህ ሃጢያታችነን ወደ መልካም ስራ እንዲቀይርልን ከፈለግን ዛሬውኑ ከልባችን እንቶብት። በነፍሶቻችን ውስጥ ያሉ ነገሮችን እንቀይር።

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) "ቀን ላይ ሃጢያት የሰሩ ሰዎችን ተውባ ለመቀበል  አሏህ ሌሊት ላይ እጁን ይዘረጋል። እንዲሁ ሌሊት ላይ ሃጢያት የሰሩ ሰዎችን ተውባ ለመቀበል ቀን ላይ እጁን ይዘረጋል" ብለዋል።

የአሏህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) አንዲት ሴት ልጇን እየፈለገች አዩ።  ባገኘችው ጊዜ እቅፍ አድርጋ ጡቷን ሰጠችው። ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ልጇን እሳት ውስጥ የምትወረውረው ይመስላችኋልን? አሏቸው። አይመስለንም አሉ። እሳቸውም ይች ሴት ለልጇ (ከምታዝነው) በላይ የበለጠ አሏህ ለባሮቹ አዛኝ ነው ብለዋል።

ሱብሃነሏህ! ይህን ልግስና ይህን የለውጥ ቃልኪዳን ካወቅን ብኋላ የተውባን ጉዳይ ችላ እንል ይሆን?  ተውበት አድርገን ወደ አሏህ መመለስን ችላ እንል ይሆን? አሏህ ሆይ! ልቅና ይገባህ ምን ያህል ርህሩህ ፣ አዛኝ ፣ ደግ ነህ። ምን ያህልስ ለጋስ ነህ።

ከራሳችን ጋር ግልፅ እንሁን እራሳችነን እንዳታለልን አንኑር!

ተውበት ከማድረግና ቀናውን ጎዳና ከመከተል የሚያግደን ነገር ምንድነው? አንዳንዶቻችን ቤተሰቦቼ ፣ ማህበረሰቡ ፣ ጎደኞቼ ልንል እንችላለን። አንዳንዶቻችን ደግሞ ተውበት አድርጌ እንደገና ወደ ወንጀሌ እንዳልመለስ ፈራሁ ፣ ወንጀሌ በጣም ብዙ ነውና እንዴት ልማር እችላለሁ? ልንል እንችላለን። ከመካከላችን አጭበርብሮ ገንዘብ ማግኘት የለመደ ሰው አመል ሆኖበት ለቤተሰቦቼና ለንብረቴ ፈራሁ፤ ማጣት አስፈራኝ ሊል ይችላል። በእርግጥ የውመል ቂያማ ላይ ጌታችንን በተገናኘን ጊዜ ይህን የምንል ወይም ይህን ምክኒያት አድርገን የምናቀርብ ይመስላችኋል? ምን ያህልስ አሳማኝ ነው? በጭራሽ አሳማኝ አይደለም። በአሏህ ይሁንብኝ እነዚህ እራሳችነን የምናሞኝባቸው የሃሳብ መሰናክሎች ናቸው። ይህ ሊገራ የሚችለው ደግሞ አሏህን በመፍራት ልጎም ነው።

ነፍስያችን ትልቅ ምኞት ካላት አካላችን የነፍስያችነን ምኞትና ፍላጎት ለመሙላት የማይፈነቅለው ዲንጋይ አይኖርም።

በዲናችን ኩሩ እንሁን! አማናችነን አሏህ ላይ አድርገን መልካም ነገር ለመስራትና መልካም ስራችነን ቀጣይነት ያለው ለማድረግ ከልባችን እንወስን። የአምላካችን እዝነትና ምህረት ቁጥር ስፍር የሌሽ መሆኑን እንገንዘብ። ይችን ፅሁፍ እያነበባችሁበት ባላችሁበት ጊዜ የሞት መልአክ ወደ እናንተ ቢመጣ በዚህ ሁኔታ ላይ ሁናችሁ አምላካችሁን መገናኘት ትወዳላችሁ? ምን ያህል ለሞት ተዘጋጅተናል። ውድ እህት ወንድሞቼ እራሳችነን አንሸሽ፤ እራሳችነን በየጊዜው ከመመርመር አንቦዝን። ምክኒያቱም ዛሬ እራሳችነን ካልመረመርን ነገ መቃብራችን ውስጥ እንፀፀታለን። ያኔ መፀፀት ምንም የሚጠቅመን ነገር የለም። ትርፉ ቁጭት ብቻ ነው።

ማወቅ ያለብን ነገር ተውባ በዚህ ወር ብቻ የተገደበ አይደለም። ተውባ በሌላም ወራት ወይም ጊዜ ሊደረግ የሚችል ነው። ይሁን እንጅ ነገ እንሞት ዛሬ ስለማናቅ ህይወታችነን የምንቀይርበት ውሳኔ ዛሬውኑ በመወሰን ተውበት አድርገን ወደ አሏህ መሸሽ ያስፈልጋል። እኛ የሰው ልጆች ሁለት ጊዜ ልንወለድ እንችላለን። አንድ ከጨለማው የእናታችን ማህፀን ወጥተን ወደ እዚህ አለም ብርሃን በተቀላቀልን ጊዜና ከሃጢያታችን ፅልመት ወጥተን ወደ ኢማን ፣ ወደ ታዛዥነት ብርሃን በገሰገስን ቀን ነው። እኛም እንዲሁ ልንሆን ይገባል።

ውድ እህት ወንድሞቼ ጎደኛ የምናደርጋቸውን ሰዎች ማንነት እንወቅ። ሁሌም ጎደኛ የምናደርጋቸው ሰዎች ወደ አሏህ ጎዳና የሚያመጡን ፣ ከሞት ብኋላ ስላለው ሐገር የሚያታውሱን ፣ በመልካም ነገር ላይ የተወዳጀናቸው ይሁኑ። ምክኒያቱም መጥፎዎች ከሆኑ የአኺራችን መበላሸት ወይም የህይወታችን መጥፎ ፍፃሜ ምክኒያት ሊሆኑ ይችላሉና። ተውበት አድርገን ዳግም ወደ ወንጀላችን እንድንመለስ መሰናከሎች ሊሆኑብንም ይችላሉ። በየትኛውም ጊዜና ቦታ እኛ የሰው ልጆች የመጨረሻ ግባችን የመፈጠራችን ሚስጥር አሏህን እስከንገናኝ ድረስ እሱን ብቻ መገዛት መሆኑን መዘንጋት አይኖርብነም።

እህት ወንድሞቼ አሏህ እንዲህ ብሎ ከገለፃቸው ሰዎች ላለመሆን እንጠንቀቅ።

**=<({አል-ቁርአን 25:27-29})>=**

**{27} ዟሊም(በዳይ) እጆቹን እየነከሰ (ምነው) ከመልዕክተኛው ጋር መንገድ ይዤ በነበር የሚልበትን ቀን አስታውስ።**

**{28} ዋ ጥፋቴ! ምን ነበር እገሌ እገሌን በፍፁም ጎደኛ አድርጌ ባልያዝኩ ነበር።**

**{29} በእርግጥ ወደ እኔ ከመጣልኝ በኋላ ከአስታዋሹ (ከቁርአን) አጠመመኝ። ሸይጧንም ለሰው ልጅ ከዳተኛ ነው።**

እህት ወንድሞቼ በሩ ሳይዘጋብን በፊት ከአሁኑ እንወስን። መከተል ያለብንን መንገድ ከመከተል አናመንታ። ወደ ጌታችን በፀፀት ስንመለስ ምን ያማረ ሐሴት ፣ ደስታ ፣ ውስጣዊ ሰላምና መረጋጋት እናገኛለን መሰላችሁ! በአሏህ ይሁንብኝ ይህን የሚያደርጉ እንጅ ጣዕሙን አያውቁም።

ቶብተን ወደ አሏህ ለመመለስ ስንወስን እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች በተውባችን ማሟለት ይኖርብናል፡፡

1. ላለፈው ነገር እንፀፀት
2. ሃጢያቱን መስራት እናቁም
3. ወደ እሱ ላለመመለስ ከልብ እንወስን
4. የሰዎችን ሐቅ ለባለቤቱ እንመልስ

ማንኛውም አይነት አስተያየት ፣ ትችትና ነቀፌታ ካለዎት በኢሜል አድራሻየ ahmedyesuf29@gmail.com ላይ ሊፅፍልኝ ወይም ደግሞ 251927790323 ላይ ሊደወሉልኝ ይችላሉ፡፡ የወጣቱ ተልዕኮ ኢስላማዊ መጣጥፎችን ለማግኘት http://youth-mission.mobie.in ይጎብኙ፡፡ ጀዛኩሙለህ ኸይረን ከሲረን!